**አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች የቤተሰብ ህይወት ትምህርት ላይ የወላጆች በምርጫ የማስተማር ፎረም - 10ኛ ክፍል**

የተማሪው ስም : ________________________________ ስልክ ቁጥር: ____________________
የአስተማሪው ስም: ________________________________ ቀን : ________________________

እኔ እዚህ ያለሁት ከተዘረዘሩት አላማዎች ውስጥ ልጄ እንዳይሳተፍ የምፈልግበትን ምርጫ እንዳደርግ ነው። ልጄ እንዳይሳተፍ በማደርግባቸው አላማዎች ላይ፣ ልጄ ያለምንም ተፅእኖ አማራጭ አሳይመንቶች እንደሚሰጡት ተረድቻለሁ። ልጄ አሳይመንት በሚሰራበት እና ለአሳይመንቱ ውጤት በሚሰጥበት ወቅት፣ በትምህርት ቤቱ ህጎች እና ፖሊሲዎች መመራት እንደሚጠበቅበት ተረድቻለሁ።

**<u>አቅጣጫዎች</u>:** እባክዎ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አላማዎች ላይ ልጅዎ እንዳይሳተፍበት የሚፈልጉትን ነገር ካለ ምልክት ያድርጉበት።

___ **10.1 ተማሪው ብስለት እንዴት በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያሉ ልጆች ላይ ተጽዕኖ እነደሚያሳድር ያውቃል።**
<u>መግለጫ</u>: የዚህ ትኩረት የሚሆነው በጉርምስና ወቅት እድገት ላይ ሲሆን፤ ይህም የሆነው ከ ራስ ገጽታ፣ በራስ መተማመን፣ አካላዊ ለውጦች፣ ሰዋዊ ፍላጎቶችን ማወቅ፣ ለስሜት የሚሰጥ ገንቢ ምላሽ፣ አወንታዊ የአዕምሮ ጤና ተግባራት፣ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት፣ የዋጋ ምንጮች፣ እና ራስን መግዛት ጋር ስለሚያያዝ ነው።

___ **10.2 ተማሪው ከራሱ እንዲሁም ከሌላ ሰው ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት የሚመለከቱ ግምቶች ላይ ስላለው አመለካከት ይገልጻል።**
<u>መግለጫ</u>: ተገቢ ጉድኝት፣ የፍቅር ቀጠሮ ወይም የቡድን ተግባራት፣ ግንኙነቶችን የመገንባት ደረጃዎች፣ ለራስ ሃሳብ መቆም፣ የፍቅር አይነቶች፣ ተግባቦት፣ እንዲሁም ግለሰባዊና ቤተሰባዊ ሃላፊነቶች ይዳሰሳሉ። ከዚህ በተጨማሪም በይነ-መረብ ላይ ስለሚመሰረቱ ግንኙነቶች የሚሰጡ ግምቶችም ይካተቱበታል።

___ **10.3 ተማሪው በሰዎች መሀል ያለ አወንታዊ ግንኙነትን ለማሳደግና ለመጠበቅ ስለሚረዱ ዋጋ፣ ግብረገብ፣ ስነ-ምግባር ይመረምራሉ**
<u>መግለጫ</u>: አለም አቀፋዊ ስለሆኑት እሴቶች ማለትም ሀቀኝነት፣ ታማኝነት፣ ራስን መቆጣጠር፣ ለራስ እንዲሁም ለሌሎች የሚወሰድ ሃላፊነት፣ ማህበራዊ ፍትህ እንዲሁም ግብረገባዊና ስነ-ምግባራዊ ስርዓቶችን መገንባት ይዳሰሳሉ። ከጾታዊ ግንኙነት በፊት ሊኖር ስለሚገባ ፍቃደኝነት ምንነትና ህጉ ይተነተናሉ። ይህም አስፈላጊነቱ በፍቃደኝነት ዙሪያ ያሉ የሌሎችን 'አይሆንም' የሚል ምላሽ በአግባቡ የማክበር ዕውቀትን ለመጨመር ነው። በተጨማሪም ኤሌክትሮኒክ በሆነ መንገድ የሚፈጸምን ጥቃትን መከላከል ላይም ያተኩራል። ተማሪዎች አወንታዊ የሆኑ ግንኙነቶችን መሰረታዊ መመሪያዎችን ይረዳሉ፤ እናም ሀይል፣ ማጭበርበር እና ማስገደድ ሲታከሉበት ግን ጥቃቶች - ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ጨምሮ ሊከሰቱ ይችላሉ።

___ **10.4 ተማሪው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን የተለያዩ ችግሮችን ለመፍታት ይተገብሩዋቸዋል ።**
<u>መግለጫ</u>: ይህ መመርያ ስድስቱ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ ያጠነጥናል። ይህም ግላዊ፣ ማህበራዊ፣ የአቻ ግፊት እንዲሁም የመገናኛ ብዙሃን መልክቶች ጋር ይገናኛል። እነዚህ ስድት ደረጃዎችም- ችግሩን ለይቶ ማወቅ፤ ሁሉንም አማራጮች ለይቶ ማወጣት፤ አማራጮቹንና ውጤታቸውን ከግላዊና ቤተሰባዊ እምነት አንጻር እነዲሁም ከማሕበረሰባዊ ዋጋ አንጻር መገምገም፤ ከአማራጮቹ መካከል ለራስ፣ ለሌሎች፣

ለመሕበረሰቡ መልካም የሆነውን አማራጭ መምረጥ፤ የተመረጠውን ውሳኔ መተግበር፣ የውሳኔውን ውጤት መገምገም ናቸው። አማራጮችን ለመገምገም የሚረዱ በማሕበረሰቡ ውስጥ ያሉ ሀብቶች ይለያሉ።

___ **10.5 ተማሪው ከጋብቻ በፊት ስለሚገረግ መታቀብ ጥቅሞች ለይቶ ያውቃል።**

<u>መግለጫ</u>: ይህ ርዕስ የዕድሜ ልክ የሆኑ አላማዎች አሁን ላይ ካሉ ጾታዊ ግንኙነትን የተመለከቱ ጫናዎች ጋር በማያያዝ ይተነትናል። በዚህ ስር የሚካተቱ ርዕሰ-ጉዳችም፤ ለወላጅነት ዝግጁነት፣ ያልተፈለገ እርግዝና ውጤቶች፣ በግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ተጽዕኖ፣ በክብር ላይ ያለው ጫና፣ የአዕምሮ ጤናና የአሁን ላይና የወደፊት ግቦች፣ ለቤተሰብ መመርያዎች የመገዛት ጥቅም፣ ትምሕርትን የመጨረስ ጥቅም፣ ኢኮኖሚያዊ ሃላፊነቶች(ግዴታዎች) ፣ እና የወደፊት ዕቅዶች እና የስራ ዕድሎች ላይ ጣልቃ ገብነት ናቸው። የግብረ ስጋ ግንኙነትን እስከ ጋበሰቻ ድረስ የማዘግየት ጥቅሞች በሰፊው ይዳሰሳሉ። ተማሪዎች ግላዊ፣ ትምሕርታዊ እና የስራ ግቦችን ይለያሉ፤ በነዚህ ግቦች ላይም ያልተፈለገ እርግዝና እና በወሲብ የሚተላለፉ በሽታዎች ያላቸውን ተጽዕኖ ይረዳሉ። ከዚህ በተጨማሪም መታቀብ ብቸኛው ሙሉ ለሙሉ ውጤታማ የሆነ እርግዝና መከላከያ መሆኑ መብራራቱ ይቀጥላል።

___ **10.6 ተማሪው ከጋብቻ በፊት ለሚደረግ የግብረ ስጋ ግንኙነት አማራጭ የሆኑ ስሜትንና ፍቅርን መግለጫ መንገዶችን ይለያል።**

<u>መግለጫ</u>: ተማሪዎች ስሜታቸውን ከ ግብረ ስጋ ግንኙነት ይልቅ በንግግር ፣ ስለ ግብ እና ዋጋ ያላቸውን ሃሳብ በማብራራት፣ ማህበራዊና መዝናኛ ግንኙነቶች እና ማሕበራው አገልግሎቶች፣ እናም አወንታዊ በሆነ አካላዊ ቅንቆ፣ አሳቢነት በተሞላበት አቀራረብ እና በሌሎች አወንታዊ ጤናማ ስነ-አዕምሮአዊ ተግባሮች እንዲገልጹ ይታገዛሉ።

___ **10.7 ተማሪው ለፍቅር ግንኙነትና ለጋብቻ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸውን ነጥቦች ያብራራል።**

<u>መግለጫ</u>: በግንኙነት ውስጥ ያሉ ደረጃዎች ማለትም፤ ጉዋደኝነት፣ የፍቅር ግንኙነት( ድንገተኛ፣ የቡድን/ሁለት ጥንዶች፣ ነጠላ ፣ የማይተዋወቁ ሰዎች፣ ጥብቅ፣ የማሕበራዊ ድሕረ-ገጽ፣ ወደ ጋብቻ የሚያመራ) እናም የአጋር መምረጥ ይለያሉ። አወንታዊና ጤናማ ግንኙነቶችን ለመገነባት የሚረዱ ደረጃዎችም ይዳሰሳሉ። መመሪያውም የሚያካትተው ፍቃደኝነት ለጾታዊ ግንኙነት ያለው አስፈላጊነት፣ የሌላኛውን 'አይሆንም' የማለት መብት ማክበር፣ የጾታዊ ግንኙነት ማህበራዊና ስሜታዊ ተጽዕኖዎች፣ እንዲሁም የጎጂ የፍቅር ግንኙነቶችን እና ለ ጥቃት አጋላጭ የሆኑ ግንኙነቶችን መገለጫ መለየት ናቸው። የራስንና የሌሎችን የግል ነጻነት እና ማይታለፉ መስመሮችን ማክበር ታይተዋል ተማሪዎቹም ይህንን የሚተገብሩባቸው መንገዶች ቀርበዋል።

___ **10.8 ተማሪው ለ ሕይወት ግብ ዕቅድ ከግምት መግባት ያለባቸውን ነጥቦች ይመረምራል።**

<u>መግለጫ</u>: የዚህ ርዕስ ትኩረት የሚሆነው ከኢኮኖሚ ጋር በተያያዘ ያሉ የስራ ዕቅዶች፣ ቀጣይነት ያለው ትምሕርት፣ ጋብቻንና ቤተሰብ መመስረትን ማስብ፣ እና የሙያ ማሳደጊያ ዕቀዶች ላይ ነው። የቤተሰብ ዕቅድ፣ የእርግዝና መከላከያንም ጨምሮ በድጋሚ ይዳሰሳሉ።

___ **10.9 ተማሪው የእርግዝና ምልክቶችን ይገልጻል።**

<u>መግለጫ</u>: መመሪያው አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ለውጦችን እና ፈጣን የሆነ በጤና ተቐም የእርግዝና ምርመራ ማድረግ ስኬታማ ለሆነ እርግዝና ያለውን አስተዋጾ ያብራራል። በማሕበራሰቡ ያሉ የመመርመር ወይም የመረጃ መስጠት አቅሞች ተለይተዋል።

___ 10.10 **ተማሪው ከጤናማ እርግዝና ጋር የተያያዙ ነጥቦችን ያብራራል።**

<u>መግለጫ</u>: ይህ የሚያተኩረው ዝቅተኛ ክብደት ያለው ህጻን እንዲወለድ የሚያደርጉ ምክንያቶችን ማለትም ፤ ማጨስ፣ ያልተመጣጠነ ምግብ፣ አልኮል እናሌሎች ንጥረ-ነገሮችን መጠቀም ወይም አግባብ ያልሆነ አጠቃቀም፣ እንዲሁም ኤች.አይ.ቪን ጨምሮ በ ግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ናቸው። ሌሎች ጥሩ እና መጥፎ ልማዶች ፤ ጥራት ያለው የእርግዝና ክትትልን ጨምሮ ሌሎች በዚህ ርዕስ ስር የሚዳሰሱ ጉዳዮች ናቸው።

___ 10.11 **ተማሪው በእርግዝና እና በወሊድ ወቅት ሊኖር ስለሚገባው ተደጋጋፊ የእናት እና የአባት ድርሻ ያብራራል።**

<u>መግለጫ</u>: የመዋያያ ርዕሱ ሁለቱም ወላጆች በቅድመ ወሊድ ሊኖራቸው ስለሚገባ ሃላፊነት፣ ስለ ዘርግንድ ተጽዕኖ፣ የጽንስ መጨናገፍን ጨምሮ ሊከሰቱ ስለሚችሉ ችግሮች፣ የወሊድ ወቅት ችግሮች፣ ጊዜው የደረሰ ግን ህወቱ ያለፈ ጽንስ መወለድ፣ ከጊዜው ቀድሞ መውለድ፣ ከወሊድ በፊት ያለ የጽንስ እድገትን ያካትታል።

___ **10.12 ተማሪው ሊገኙ የሚችሉ የወሊድ አማራጮችን ያብራራል።**

<u>መግለጫ</u>: ስለ ወሊድ ለማስተማር የተዘጋጁ የትምሕርት ማገዣዎች በዋነኝነት ጥቅም ላይ ይውላሉ። የወሊድ አማራጮች ይገመገማሉ።

___ **10.13 ተማሪው የወሊድ ሒደትን ይለያል።**

<u>መግለጫ</u>: የወሊድ ሒደት ደረጃዎች ሰስቱን የምጥ እና የወሊድ ደረጃዎችን ያጠቃልላሉ። እነርሱም የማህጸን ግድግዳ መለጠጥ፣ ወሊድ፣ እና የእንግዴ ልጅ መውጣት ናቸው።

___ **10.14 ተማሪው ውጤታማ ወላጅ ለመሆን የሚያስፈልጉ ክህሎቶችንና አመለካከቶችን ይተነትናል።**

<u>መግለጫ</u>: ስለ ልጅ አስተዳደግ(ወላጅነት) ያሉ አመለካከቶች ይቃኛሉ። መመርያው በህግ የተገለጹ የተለያዩ የልጅ አስተዳደግ መንገዶችንም ይጨምራል። ተማሪዎቹ ሊኖራቸው የሚፈልጉትን የወላጅነት ክህሎት የመለየት ዕድል ይኖራቸዋል። ተማርዎቹ ስለወላጅነት ሃላፊነት አስፈላጊነት ይረዳሉ። እንዲሁም ጽኑ የሆነ ግንኙነት ወይም ትዳር ለወላጅነት ስለሚኖረው ጥቅም፣ ስለፈተናዎቹ፣ ስለሃላፊነቶቹና ስለሚነረው ዋጋ ይገነዘባሉ። ተማሪዎቹ እንደወላጅ ሊያገኙት ስለሚችሉት ማሕበረሰባዊና ቤተሰባዊ ድጋፍ ለመለየት ይችላሉ። በተጨማሪም ወላጅነት የአዕምሮ ጤና ለይ ስለሚኖረው አወንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች ለመረዳት ይችላሉ።

___ **10.15 ተማሪው ከወሊድ ቀጥሎ ስለሚኖሩ ማስተካከያዎች ይገልጻል።**

<u>መግለጫ</u>:ህጻኑ ልጅ እንደ ደስታና ፍቅር ምንጭ ይገለጻል፤ በሌላ መልኩ ግን ልጁን የሚንከባከበው ቤተሰብ ላይ ያለው ተፅዕኖ ከገቢ አንጻር፣ ከትምሕርት ዕቅድ አንጻር፣ከመዝናኛና ከእንቅልፍ ሰዓት አንጻር እና ቤተሰቡ እርስ በርስ ካለው ግንኙነት አንጻር ይመዘናል።

___ **10.16 ተማሪው ግለሰብን እንዲሁም ቤተሰብን ለማገዝ የሚችሉ የሕብረተሰብ ኤጀንሲዎችንና ሃብቶችን ዝርዝር ያዘጋጃል።**

<u>መግለጫ</u>: በዚህ ዝርዝር ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ የማሕበረሰብ ሃብቶች የአዕምሮ ጤና ተቆማት፣ ማህበራዊ ተቆማት፣ የሐይማኖን አደረጃጀቶች፣ የግል ኤጀንሲዎች፣ የቀን መውያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የአረጋውያን መንከባከቢያዎች፣ እና የጤና ክፍል ናቸው። ጥቃትን ለመከላከል፣ የህጻናትን ጉልበት ብዝበዛ፣

የህጻናት ጾታዊ ጥቃት፣ ጾታዊ ጥቃቶች፣ የህጻናት ጠለፋ፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውርና ራስን ማጥፋት የመሳሰሉትን ለመከላከል ነጻ የስልክ መስመሮች ተለይተዋል።

___ **10.17 ተማሪው ቤተሰባዊ ሕይወት እንደ መሰረታዊ ማሕበረሰብ አካልና ማንነትን እንደመገንቢያ አወንታዊ ነጥብ ይመለከተዋል።**

መግለጫ: መመርያው የቤተሰብ ተግባርና ሁኔታን በተለይም እርስ በርስ ባለ መስተጋብርና በቤተሰባዊ ግንኙነት ዋጋ ላይ ያተኩራል። ቤተሰብ ለማንነት ግንባታ ሒደት እና እንደ ባለትዳርም ሆን እንደላጤ ለአዋቂነት ሕይወት መዘጋጃ የመጀመርያውና መሰረታዊው ነጥብ ነው። ቤተሰብ ከሕብረተሰብና ከ ዓለም ጋር ያለው ግንኙነትም በሰፊው ይዳሰሳል።

**ትምህርት ቤታችሁ በወሰነው ቀን መሰረት ይህንን ቅፅ በመሙላት ለርእሰ-መምህሩ እባክዎን ያስረክቡ**

የወላጅ/የአሳዳጊ ፊርማ: ________________________________________ ቀን: __________